# የኤርትራ የመገንጠል መዘዝና ከኢትዮጵያ ጋር የቀዶ ጥገና ግንኙነት

ለአከ ገብረፃድቅ
ነሐሴ 14፡ 2001 ዓ ም

## <u>ክፍል አንድ</u>

ከዚህ ቀደም (March 15, 2009) በፕሮፌሰር ተስፋፅዮንና ዳኒኤል ክንዴ አስተባባሪነት የኢትዮጵያና ኤርትራ ግኑኝነት ማወያያ ስብሰባ መካሄዱ ይታወሳል። ለውይይቱ የቀረበ የሁለቱም ፅሁፎችም በኢንተርኔት ለአጭር ጊዜ ተለጥፎ በነበረበት ጊዜ ለማንበብ እድል አግኝቻለሁ።

በጥላቻ ፖለቲካ የተለያዩትና የተጻሙት ሁለቱ ህዝቦች እዚህ ደረጃ ላይ መገኘታቸው አስከፊ ነገር ነው። ኤርትራ ከተገነጠለች ወዲህም ለአካባቢው አገሮች የሁከት መንስኤ ሆና ቆይታለች። ያለው መንግሥት በሥልጣን ኖረም አልኖረ ኤርትራ ለወደፊቱም በዚሁ አፍራሽ ሚና እንደምትቀጥልበት ካላት ስትራተጅያዊ ስፍራና ጉርብትና፣ ፀበኛ ማህበረ-ፖለቲካዊ እንዲሁም ስነልቦናዊ ባህርያት፣ ቁጠባዊ ችግር፣ ወዘተ አኳያ መገንዘብ ይቻላል። ኤርትራን ከዚሁ አሉታዊና አውዳሚ ሚና ማዳን የሚቻለው ከኢትዮጵያ ጋር ግኑኝነትዋን ስታድስ ሊሆን ይችላል።

ይሁንና ግኑኝነቱን የማሻሻል ዓላማ ተገቢ ቢሆንም ገና ለገና ከአሁኑ መደረግ አለበት የሚሉ ሰዎች ስለማይጠፉ ጉዳዩን ከሕዝብ የመወሰን መብት ነጥቆ ወይም በስተጀርባ መፍታት መሞከር ላሉት አውዳሚ የኢትዮጵያና ኤርትራ ስርዓቶች የመገልገያ መሣርያ በመሆን ወቅቱ ያልጠበቀ ግኑኘነት መሻት የተለመደውን ውድቀት የሚጋብዝ በመሆኑ በጥንቃቄ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያም ይሁን የኤርትራ ምሁራን ሰፊውን ህዝብ እኛ እናውቅልሃለን በማለት እራሳቸው ተማጓች፣ ጠበቃ፣ ዳኛ፣ አፈቀላጤ፣ እና ጠቅላላ የሕዝቡን ሁሉም መብቶች በብቸኝነት ወሳኞች በመሆን ብዙ ፖለቲካዊ ጉዳዮችና በሕዝቦች መካከል ያለውን ግኑኝነትና ዝምድናም ሲያበላሹ ቆይተዋል።

የፕሮፌሰር ዳንኤል ፅሁፍ ሳነብ ይህ ዓይነት ጠባያት ስለሚታዩበት የኢትጵያ ሕዝቦች ግንኙነት በባሰ የሚያደፈርስ በመሆኑ የሚረብሽ ጉዳይ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። አሁንም ቢሆን የሚደረገው መልካም ጥረት ባለው የጦርነት ውጥረት መሃከል ያልታለመለት አቅጣጫ ሊይዝ ስለሚችል በበኩሌ ይህ ያነሳሳኝ ዋና ምክንያት በጥንቃቄ መታየት እንዳለበት በማስገንዘብ ያለኝን አስተያየት እሰጥበታለሁ።

ፕሮፌሰር ተሰፋፅዮን የኤርትራን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ ፈር የያዘ ክርክር ሲያቀርቡ ፕሮፌሰር ዳንኤል ግን ከግንኙነቱ ውይይት ጋር ምንም ግኑኝነት የሌለው፣ ተገቢ ያልሆነና አወዛጋቢ ጉዳዮች ላይ ብዙ አትተዋል። ይልቁንም ለኢትዮጵያ የሚረዳ ሳይሆን የሚጎዳ ብዙ የውስጥ ፖለቲካዊ ጉዳዮች መነሳት በሌለበት መድረክ ላይ ተናግረዋል። ያቀረቡት ሃተታ እውነታና ታሪክን የተመረኮሰ፣ በማስረጃም የተደገፈ ሳይሆን በስሜትና ጥላቻ ግፊት ያሉት ብዙ ነገር ምን እንደሆነ (ወደ ዋናው የኢትዮጵያና ኤርትራ ግኑኝነት ሁኔታ ከመግባቴ በፊት)

ካነሱዋቸው ነጥቦች አኳያ ያለኝን አስተያየት በዝርዝር አቀርባለሁ። እውነቱን ለመናገር፣ ብዙዉን ያሉት ነገር ለትችትም የሚበቃ አይደለም፤ ፅሁፋቸው እውነትን የሚያጣምም፣ እርስ በርሱ የሚቃረን፣ አድልዎ፣ ግድፈት፣ ስህተት፣ ውሸትና፣ ማጋነን የተሞላው ነው። ይህ አይነት ባህሪ የሚታይበት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል ያስከተለው ውድቀትና ኪሳራ ለመጋፈጥ እንዲቻል ግን እንደዚህ የሚፃፉ ሃሳቦች በመተቸት ችግሩ ምን ላይ እንደሆነ ጠልቆ መመርመርና መወያየት አስፈላጊ ነው እላለሁ። የሳቸውን ያህል ትምህርት ስለ ሌለኝ ደፈረኝ አይበሉኝ እንጂ ስህተቶቹን ለምን ስህተት እንደሆኑ ዘርዝሬ አስቀምጣለሁ።

ይህ ስል፣ ትችት መስጠትና መቀበል ባህል ባልሆነበት በተማረው የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ቀላል እርምጃ እንዳልሆነ በመረዳት የምሰጠው ትችት ላይቀበሉት ይችላሉ። አብዛኛው የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ከትግሉና ውይይቱ ለምን ራሱን ያገላል ብንል ምክንያቱ ግልፅነትና ቀናነት በመታጣቱና መድረኩ ከፋፋይ ፖለቲካ በሚያራምዱ ሓይሎች ስለተጣበበ ነው። ቀና አመለካከት ያለው ሰው በስብሰባ እንካ ስላንካውን ተለዋውጦ ወይም ተሰድቦ ህሊናው ቆስሎ መመለስ አይፈልግም። ለአብነት ያህል ለምን የትግራይ ሕዝብ ወይም ተወላጆች በትግሉ አይሳተፉም? ያለው መንግሥት ስለሚደግፉ ነው የሚሉ ብዙዎች ስላሉም፣ ዋናው ምክንያት ይልቅ ከላይ የጠቀስኩት እንደሆነ ጥርጥር የለውም። ሆን ተብሎም እንዲርቅ የሚያደርጉ ሃይሎችም አሉ።

ሌላው ከመሠረታዊ ችግሮች አንዱ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል ብዙ ሰዎች ስለ ሚፅፉት ወይም የሚናገሩት ፖለቲካ በሃሳብ ደረጃ ሳይሆን በላቀ ደረጃ በእምነት የምይዙት የማይነካ ጉዳይ ስለሚሆን የመወያያ በሩን ከወዲሁ ይዘጋሉ። የወያነ፣ የኢህአፓ፣ አነግ፣ ወዘተ አባላት ወይም ደጋፊዎች እስከ ዕለተ ህልፈታቸው የሁለት ዋለታዎች ተፃራሪ ፖለቲካን ይከተላሉ። አመለካከትን መቀየር የሚባል ባህል የላቸውም። ብዙ ሰዎች የፖለቲካ እይታቸው ካረጁ-ያፈጁ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ተጠምዶ የቀረ ነው። አንዳንዴም ከስማቸው በፊት ኢህአፓ፣ ጀብሃ፣ ወዘተ እንደሆኑ ማንነታቸውን ይገልፁበታል። ከኮሚኒስት ደርግ የተወረሰ ውሸትን የመፍጠርና የማስረፅ እንዲሁም ሓቅን ሓቅነቱ እስኪበልዝ ድረስ ማጋነን የመሰሉ የውይይት እድል ዘጊ አመሎችም ይገኙባቸዋል። ያም ሆኖ ግን ወደ አደባባይ የሚወጣ የጋራ መብትንና አገርን የሚነካ ንግግር፡ በተለይም የፖለቲካ ጉዳይ የሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ ጉዳይ ነውና በአግባቡ ከመተቻቸትና ከመተራረም ሌላ ይህን አስከፊ ባህል የሚቀየርበት ሌላ ዘዴ አይኖርም።

1. የፕሮፌሰር ዳንኤል በትግራይ ላይ ያነጣጠረ የብሄረሰብ ሽኩቻ ፖለቲካ

እንግዲህ ፕሮፌሰር ዳንኤል ያነሱዋቸው በከፊል በጥቅስ ያስቀመጥኩዋቸውን ነጥቦችም በዝርዝር እንመልከት፡-

> *ሀ- "ለምሳሌ ያህል ከሃዘሞ (አከለጉዛየ) ተነስቶ <u>ወሎ</u> ድረስ ለግጦሽ በየ ዓመቱ ይመጣ የነበረው ከብት ውሃና ሳሩ ሁሉ የት እንዳለ በትክክል ያውቀዋል። እንደዚሁም ከሠራየና ጋሽ ሰቲት ተነስቶ በየዓመቱ <u>ጎንደር</u> ድረስ ሚመጣው ከብት*

የግጦሽ ሰፈሩን ጠንቅቆ ያውቅ ነበረ። ለምሳሌ ያህል ሰቲት ሑመራ፣ ባናት፣ ባሕረ ሰላም፣ ንጉዲ፣ አርማጭሆ፣ ኮረደም ሊጠቀሱ ይችላሉ።" (ገፅ ፫)

ከሃዘሞ ወሎ ድረስ የሚጓዝ የኤርትራ ከብት ምንኛ አዋቂና አስተዋይ መሆኑ ከማጋነን በተቀረ ትግራይን ዘሎ እንዴት ወሎ ድረስ ከብት ለግጦሽ ሊሰደድ እንደሚችል የሚገርም ነገር ነው። የኤርትራ "ከበሳ" ገበሬ ዘላን እንዳልሆነም እናውቃለን፤ ቀዋሚ ቤተክርስትያንና ማህበረሰብ እንዲሁም የመሬት ይዞታ ያለው ነው።

በእርግጥ ከፈደሬሽኑ በኋላ በአንድ ወቅት በሓማሴንና አከለጉዛይ ከመሬት ጥበት በተጨማሪ ድርቅ በመከሰቱ ብዙ ህዝብ ያልቅ ስለ ነበር የትግራይ መኳንንት ተወያይተው ይህን ወንድማማች ህዝብ ለመርዳት ተብሎ ገበሬዎችን ወደ ትግራይ የሽረ ለም መሬቶች እንዲሰፍሩ መፍቀዳቸው ይታወቃል፤ እንጂ በዘፈቀደ ባለ ከብት ድንበር ዘሎ በየኣመቱ የሰው መሬት ላይ የሚያከርምበት ሁኔታ አልነበረም። ያ ቢሆንማ ኖሮ የኤርትራ ሰዎች የመሬት ይዞተቸውን በማረጋገጥ መሬቱ የኤርትራ በሆነ ነበር። በዚህ ሰበብም ነው ውስን የኤርትራ ተወላጆች በትግራይ ዳርቻ ወረዳዎች በመገኘታቸው ሻዕብያና ጀብሃ "የይገባኛል" ጥያቄ መግፋት የጀመሩበትና ይህም ለማሳካት ብዙ ዘዴዎች ሲጠቀሙ የቆዩት። የተጠቀሙት ዘዴም አንዱ አሁን ካሉት የወያነ መሪዎች የትግራይን መሬት ቆርሶ ለመስጠት በሚስጥር ፅሁፍ በመፈራረም፣ ለዚሁም የሚያሳካ እርምጃ ላይ በመስማማት ለምሳሌ በባድመ አካባቢ ቀረጥ አከፋፈል ላይ ሕዝቡ በሁለት ማለት ለሻዕብያና በነሱ ወገን እንዲከፈል ማድረግ ነበር። ሌላ ቀርቶ እጅግ ከፍተኛ የህዝብ ሽፋን ያለበትና የመሬት ይዞታ የተጣበበበት የዛላንበሳ ወረዳ በ1970 ዓም ሻዕብያ በትዕቢት የኤርትራ ተጎራባች ወረዳ ገበሬዎች ከታጣቂ ሰራዊት ጋር በመላክ የትግራይ የእርሻ ይዞታን ማረስ ሲጀምር ብጥብጥ ተነስቶ ነበር ሊገታ የቻለው። ሻዕብያ ይህን ሲያደርግ የወያነ መሪዎች ልብ በደንብ በመረዳቱ ባይሆን ኖሮ እንደዚህም ባልደፈረ ነበር። በዛን ወቅት አሁን "ወያኔ" የሚባለው በመለስ የሚመራው ድርጅት ድርጊቱን ለመቃወም ጣቱንም አላነሳም።

> ሉ- "ከሻቢያ ባገኙት የጦር መሣሪያ በመመካት፣ የወያኔ መሪዎች ሑመራን፣ ወልቃይትና ጠገዴን ከጎንደር ወስደው፣ ራያ አዘቦንና አላማጣን ከወሎ ከነጠቁ በኋላ የሚያሥሩትን አሥረው፣ የሚገድሉትን ገድለው ኗሪውን ሕዝብ በማባረር 650000 የሚሆነውን የትግራይ ገበሬና ወታደር በእነዚህ መሬቶች ላይ አሥፍረው ይገኛሉ። ...አንድ ሦስተኛ የሚሆነውን ለምና ታሪካዊ መሬት በማንአለብኝነት መንፈስ በመነሣሣት ለሱዳን መንግሥት አስረክበዋል። ይህ ድርጊት የታላቋ ትግራይ ሪፓብሊክን መቋቋም ሲያውጁና ሲገነጥሉ፣ ሱዳን ከጎናቸው እንዲቆም የተሰጠ ጉቦ ነው።" (ገፅ ፯)
> "…..ትግርኛ ለመናገር የሚችለውን ሰው ሁሉ የታላቋ ትግራይ አካል መሆን አለበት ብለው ያምናሉ።" ወዘተ (ገፅ ፯)

ተመልከቱ እንግዲህ፤ ዳንኤል ክንዴ ወቅታዊ ታሪክንና እውነተኛውን መንገድ ስተው በጨለማ ጉዞ በዳሰሳ ሲሄዱ፤ ከየትኛው መፅሃፍ ባነበቡት ነው "ወያኔ" ከሻዕብያ መሳርያ ተውሶ "የጎንደርን መሬት" የያዘው? አንደኛ ነገር፣ ይህን እጅ እጅ

ያለውን የተደጋገመ ወሬ ሲፅፉ ለኣእምሮ-ቢስ አክራሪ ብሀርተኞች ሰሙናዊ የፖለቲካ ፍጆታ ተብሎ የታሰበ ካልሆነ በስተቀር ወያነ ከሻዕብያ የብድር መሳርያ ታጥቆ ኣያውቅም። እንድያውም በመጀመርያዎቹ የትግል ዘመናት ቀዋሚ ወታደራዊ ሰፈር ስላልነበረው ወያነ የማረካቸው ከባድ መሳርያዎችና ተሽከርካሪዎች ለጀብሃና ለሻዕብያ ነበር ሲለግስ የነበረው። ወያነ ኣዲስ ኣበባ በሻዕብያ ታጅቦ፣ መሣርያ ታጥቆ፣ ወዘተ ለስልጣን ደረሰ እንደሚሉት ዝባዝንኬ ቢሆን ኖሮ ግንቦት 7፣ አርበኞች ግንባር፣ ኦነግ፣ እንደነ ቅጣው እጅጉ የመሰሉ ከሃዲ ግለሰቦችና ድርጅቶች ለምን ስልጣኑን እስካሁን ኣልጨበጡም? የመለስ ዜናዊ መንግሥት ወታደራዊ ሃይሉ ከደርግ ጋር እንኳ ማወዳደር ኣይቻልም። ከሓዲውን የመለስ ዜናዊ መንግሥት የሚወገድበት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ህብረት ከመሻት ይልቅ ይህ ራስን ኣታልሎ ሌላዉን የማታለል የስነልቦናና የኣእምሮ ቀውስ ዋናው የትግሉ እንቅፋት ሆኖ እንዲቀጥል ገና እየተገፋበት ነው።

ሁለተኛ፣ ለሱዳን የተለገሠው መሬት የትግራይንም ጨምሮ ነው። መተማ ዓፄ የውሓንስ የተሰዉበት የኢትዮጵያ ቅዱስ መሬት ነው ለሱዳን የተሰጠው። እንዴት ያለ ትንተና ተጠቅመው ነው የትግራይን መሬት ለባእዳውያን፣ ለሱዳንና ኤርትራ እያደለ ያለው የመለስ ዜናዊ የክሕደት ስርዓት ታላቅዋ ትግራይን ሊመሠርትበት ነው የሚሉት? መለስ ዜናዊ ስለ ኤርትራ ካለሆነ ስለ ሌላ ነገር ቅንጣት ግድ የለዉም። ኢትዮጵያን ከመጠን በላይ እንደሚጠላም የማያሻማ ሲሆን ከኣፍቅሮተ-ኤርትራ የማይነጣጠሉ ባህርያትም ናቸው። እየፈፀመ ያለውን ኣገርን የመቆራረስ ዓላማ ከዚህ ውጭ ከሆነ እውነቱን ለመረዳት የስነልቦናና የኣእምሮ ተማራማሪን ልዩ ችሎታና ሞያ የሚፈልግ እንቆቅልሽ ነው። የመለስ ዜናዊና ግብረኣበሮቹ ትውልድና የቤተሰብ ኣመጣጥ ታሪክም ጠንቅቆ ማወቅን ያሻል። ያለን ስርዓት ዲሞክራስያዊ ቢሆን ኖሮ የመለስና ተከታዮቹ የዜግነት ዕጣ ኤርትራ በተገነጠለች ማግስት በለየለት ነበር።

ይህ መንግሥት በኣገርና ህዝብ ላይ ለሚፈፅማቸው ወንጀሎች የሚቆረቆረው ከትግሬው በቀር ሌላው ኢትዮጵያዊ እንደሆነ ኣስመስሎ ማቅረብም ትልቅ ስህተት ነው። ስለ ምንስ ይገርማቸዋል መለስ ይህን ኣይነት ክህደት መፈፀሙ? ብዙ ከሃዲዎች ከጠላት የኤርትራ መንግሥት ሲዶሉቱ ይውሉ የለም እንዴ? የውስጥ ጠላት ለማጥፋት የኢትዮጵያን ጠላት ኣይጋብዙበትም። የመለስ ዜናዊ መንግሥት ደግሞ የኣፄ ምንሊክ ትንሳኤ-ሙታን መንግሥት ነው። እሳቸው የጀመሩት ኣገርን የመቆራረስ ሥራ ነው ከፍጻሜ በማድረስ ላይ ያለው። ኣፄ ምንሊክ በኣድዋ ጦርነት ወቅት ጣልያን ከዓዲግራት ሰራዊቱን እንዳያስወጣና ባለበት እንዲፀና በድብቅ በደብዳቤ ይማፀኑት እንደነበር በታሪክ የተዘገበ ነው። እንደ ተግባራቸው ቢሆን ኖሮ የዛሬይቱ ኤርትራ ትግራይንም እንደ ጣልያን ግዛት ይጨምር ነበር። መለስና ምንሊክ ጊዜ ይለያያቸው እንጂ የፈፀሙት ኣገርን የመሸጥ የክህደት ወንጀል በኣደባባይ ጎን ለጎን የሚያሰቅላቸው ወንጀል ነው። የኢትዮጵያ ኣስቸጋሪ ታሪክ ለመረዳት እንግዲህ ከተክለፃዲቅ መኩርያ "የቅንብር ታሪክ" ፅሁፎች ከማንበብ ኣልፎ ሌላ ትልቅ ስራ ይጠይቃል።

ሦስተኛ ነገር፣ "ቋንቋ የመገናኛ፣ የጥናትና ምርምር መሳርያ ነው" ወዘተርፈ፣ ካሉ በኋላ ሰዉ ትግርኛ ቢናገር ለምን መሬቱ ወደ ትግራይ ይጨመራል ለማለት ብዙ

ዝባዝንኬ ብለዋል። ቋንቋ የመገናኛ ወይም ለአንድ ህብረተሰብ የመናገርያ መሳርያ ብቻ አይደለም፤ የማንነቱ፣ ታሪኩና ባህሉ መሠረት ነው። የሰዉም ብቻ ሳይሆን ስለ መሬቱንም ታሪክ ብዙ የሚለው ነገር አለ። ወደ ትግራይ የተመለሱት መሬቶችም የሚመሰክሩት ይኸንኑ ነው።

ስለ ምንስ በወልቃይት ያሉ ሰዎች ትግርኛ መናገር ቀርቶ ትግርኛ ተናጋሪዎቹ አማርኛ ተናጋሪ አልሆኑም ለሚለው መልስ አልሰጡበትም። ይህ አስቸጋሪ የሆነባቸው ጥያቄ ሊመልሱት አልፈለጉም። እነኚህ ከጎንደርና ወሎ ወደ ትግራይ የተመለሱት ወረዳዎች በማእከላዊ መንግሥት ከትግራይ ተነጥቀው ወደነዚህ ክፍለሃገራት የተደመሩ ስለ ነበሩ ይህንን ፀሓይ የመታው ሓቅ ሊነግሩን ስላልፈለጉ ነው። የህወሓት የትግል መነሻም አንዱና ዋነኛው ምክንያት እነኚህ የትግራይ መሬቶች የመቁረስ ሕገወጥ ተግባር የጠራራ ፀሓይ ዝርፍያ ስለሆነ ለማስመለስ ነበር። እንድያውም ከደቡብ የሚገኝ ከፊል የትግራይ መሬት በአብዛኛው በአማርኛ ተናጋሪ ተይዞአል ተብሎ ከወሎ ጋር ተርፎአል። ይህ የትግራይ የደቡብ ታሪካዊ መለያ ድንበር አልወሃ ምላሽ ይባላል።

ፕሮፌሰር ዳንኤል ይህን ታሪክ ሰላስቸገራቸው ይመስለኛል ስለ ቋንቋ የራሳቸው ፅንሰ-ሃሳብ በመፍጠር ዙርያ ጥምጥም መሄድ የመረጡት። ስለ ቋንቋ ካነሳን ላይቀር፣ ንጉሥ ሃይለስላሴ መሬቶቹን እንደነጠቁ ብዙ አማርኛ ተናጋሪ ወገኖቻችን የማስፈር ዘመቻ አካሂደውበታል። የወልቃይት፣ ፀለምቲ፣ ሑመራ፣ ዓደርቃይ፣ ዓዲ ረመፅ፣ ደጀና፣ ወዘተ መሬቶች ብንወስድ ታሪኩ ይህ ነው። የቦታዎች፣ ወረዳዎችና አምባዎች ስም በሞላ በትግርኛ የሚጠሩት መሠረታዊ ታሪካቸው ትግራይ ስለሆነ ነው። ዳንኤል ክንዴ ግን ለማጭበርበር ቦታዎቹን ፀለምትን፣ ጨለምት፣ ወዘተ ብለው ወደ አማርኛ ለመቀየር ሲሞክሩ ሓቅንና ታሪክን በማባከን አይናችሁን ጨፍኑና ላሞኛቹህ ማለታቸው አሳፋሪና ኢ-ምሁራዊ ምግባር ነው።

> ሐ- እሳቸው እንግዲህ "…ወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ትግርኛ ተናጋሪው 5% ብቻ ነው። 95% አማርኛ ተናጋሪ ነው። ትግርኛውም የተማረው ከኤርትራኖች ነው። ከትግራይ ጋር ምንም ዓይነት ግኑኝነት የለውም።" ነው የሚሉት። (ገፅ ፷)

እዚህ ላይ 95% አማርኛ ተናጋሪ ነው ብለዋል። እላይ ከጠቀሱት፣ የአካባቢው ነዋሪ ትግርኛ በመናገሩ ብቻ ወደ ትግራይ ለምን ይጨመራል፣ ካሉት ጋርም ይቃረናል። አሃዞቹን ብናሰላ ደግሞ የተባለው አካባቢ ህዝብ 13 ሚሊዮን ደርሶአል ማለት ነው። ምክንያቱም ቀደም ሲል እንዳመለከቱት ቢያንስ 650 ሺህ ትግርኛ ተናጋሪ አለ ነው የሚሉትና የተቀረው 95% አማርኛ ተናጋሪ 12.3 ሚልዮን መሆኑ ነው። ሌላው ቅሌት የተፈሞላበት አባባላቸው አማራው "ትግርኛውን የተማረው ከኤርትራኖች" ነው የሚል ነው። በየትኛው አገር ነው የኤርትራ ህዳጣኑ ከብት እረኞች ብዙሓኑን አማራዎች ቋንቋዉን እንዲማር የሚያስገድድበት ሁኔታ? እንደ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ ወይም ፐርቱጋል ቅኝ ገዢ መሆናቸው ነው? ደግሞም እንደ አባባላቸው ከሆነ መሬቱ ለኤርትራ ይገባል ማለት ነው። ይህ አይነቱ አስተሳሰብ የጎደለው አባባል ለትእዝብት የሚተርፍ ነው።

እውነተኛው ታሪክ፣ በዛው የነበረ የትግራይ ተወላጅና ባላባት ህዝብ ብዛት ወሳኝነት ስለነበረው መጤው ህዝብም ሌላ አማራጭ ስለማይኖረው ባህሉንና ቋንቋዉን መላመድ ተገዶኣል። ለዚህ ነው የኣማራ ተወላጅነት ያላቸው ሰፋሪዎች ትግርኛ የሚናገሩትና ማንነታቸውን ግን ከጎነደር ጋር ማዛመድ የሚሹት። ሰፋሪዎቹ ከየት ናቸው ብንል ከጎንደር ብቻ የፈለሱ ኣልነበሩም፣ ከጎጃምም በብዛት ይገኙባቸዋል። ትውልዳቸው ወደ ጎንደር ወይም ጎጃም ካልተሻገረ በቀር በትግራይ መሬት ከሦስት ወይም ኣራት በላይ ኣልፈው መቁጠር ኣይችሉም፤ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነውና። ስለዚህ የጎጃም ገበሬ ሰፋሪዎች ለምን ጎንደርን ዘለው መጡ የሚለውንም መጠየቅ ያስፈልጋል። ይህን ሓቅ ወደ ኣእምሮ ለማስረፅ ይረዳ እንደሆን የኣሁንዋ "የጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ባለቤት ቀዳሚት እመቤት ኣዜብ መሥፍን" ራስዋ የዚሁ ሰፋሪ ህብረተሰብ ትውልድ ናት። የኢህኣፓ ደጋፊ ስትኖር፣ ወደ ወያነ የተቀላቀለች በኃላ ነው። እናትየዋ በወልቃይት ዓዲ ረመፅ የምትባል ትንሽ ከተማ በጠላ ሽያጭ የሚተዳደሩ እንደነበሩ ይታወቃል። ኣባትዋ ባይታወቅም (እርስዋም ኣታውቀውም ማለቴ ነው) መሥፍን ስለ መልካም ስም ምርጫ የተለጠፈ ካልሆነ በቀር ትክክለኛ ስሙ ኣይታወቅም። ኣባትየዋ ሱዳናዊ ነውም ይባላል። እግረመንገዳችንም ትምህርት ይሆን ዘንድ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ስልጣን ላይ የተቀመጡ ሰዎች ማንነት እንገንዘብ።

ሌላው ዳንኤል ክንዴ ማወቅ ያለባቸው ነገር እነኝህ የምንነጋገርባቸው የምዕራብ ትግራይ መሬቶች በራእሲ ደጌና ይተዳደሩ የነበሩ ናቸው። የሽረ ወረዳዎች ጭምር በኣራቱ ወንድ ልጆቻቸው የሚጠሩና የሚተዳደሩ ነበሩ። ራእሲ ደጌና እስከ ዛሬ ድረስ ራስ ዳሽንና ደጀና የሚባል (የወያነ ዋና ወታደራዊ ሰፈር የነበረ) የወልቃይት ቦታዎችም በስማቸው ይጠራሉ። ራእሲ ደጌና ትውልዳቸው ከምስራቅ ትግራይ ከዓጋመ ኣውራጃ ሲሆን የተወለዱትም ከዓዲግራት ወጣ ብሎ የሚገኝ ገጠር ሌላ ስሙ "እንዳ ደጌና" ተብሎ በሚታወቅ ነው። የታሪኩን ስር መሠረት ለማስያዝ ያህል ራእሲ ደጌና የተወለዱበት ኣካባቢ ሰርወ-ትውልድ እንደሚከተለው ነው፤ ራእሲ ደጌና -> ኣከሎም -> ጋድ -> ዳን -> ንኡስ ኣከሎም -> ክፍለኪኤል -> ኣቢሞስ -> ኣዛይ ገደ -> ክፍለማርያም -> ማርያማዊት -> ወልደኣረጋዊ -> ገርግስ -> ኣበሰሎም -> ሎቱ -> ገብረመስቀል፣ ወዘተ ይቀጥላል። ይህ ትውልድ ራሴ የምጋራው ሲሆን እንግዲህ ዘመኑ መቸ እንደ ነበር ለማወቅ ወደ ኃላ ተመልሶ የማስላቱን ሥራ ለፕሮፌሰሩ እተወዋለሁ። በጎንደር ዘመነ መንግሥት ጊዜ ሆኖ እንደሚያገኙትም እርግጠኛ ነኝ። በኔ ኣመለካከት መሠረታዊ ታሪክንና ሀቅን በመካድ እንደኮሚኒስት ስርዓት በጭፍን መዋሸትና ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ የሚደረግ የማጋነን ሥራ ኣገሪቱን ሰላም የሚነሳና ለባሰ የእርስ በእርስ ግጭት ብሎም መነጣጠል ከመጋበዝ በቀር ሌላ ፋይዳ የለውም።

> መ- "… የኢትዮጵያንና የኤርትራን መቀራረብ የሚቃወሙበት ምክንያት የታላቋ ትግራይን እቅዳቸው ስለሚያበላሽባቸው ነው።" (ገፅ ፺)

የሚቃወሙት እነማን ናቸው? የመለስ መንግስት፣ ዓረና ትግራይ፣ ወይስ የትግራይ ሕዝብ ጭምር? ፕሮፌሰር ዳንኤል ለይተው ሳያስቀምጡ ሁሉም በጅምላ ተጠያቂ በማድረግ በሃተታቸው ያቀርባሉ። ከኤርትራ ጋር ያለ ግኑኝነት በተመለከተ የችግሩ መንሥኤ ምን እንደነበር ተመልሶ መዘርዘር ኣስፈላጊ ኣይመስለኝም፤ ኤርትራ

ከኢትዮጵያ የነበራት በሽተኛ ግኑኝነት ዋና ምክንያት ግን የኢትዮጵያ ሉኣላዊነት መደፈር ሲሆን በማቋረጥ ወሳኝ ሚና የተጫወተው ከህወሓት የተነጠለው ኣመራርና የትግራይ ሕዝብ ነው። ኢሳያስ እሺ ቢል ኖሮ መለስ ወደ ነበርንበት ሊመልሰን ከድንበሩ ግጭት በኃላ ባለ ኣምስት ነጥብ ሃሳቦችን ኣቅርቦለት ነበር። በድንበሩ የንግድ ግኑኝነት ችግሮችና የሻዕብያ ዝርፍያና ግድያ ወንጀል ሲበዛ ነው ሕዝቡ ከጦርነቱ በፊት በኤርትራ ላይ በሩን መዝጋት የጀመረው። ኣብዛኛው የትግራይ ሕዝብ የኤርትራ ምንም ዓይነት የፍጆታ ዕቃ እንዳይጠቀም ማእቀብ ጥሎ ነበር። መለስ ከጦርነቱ በኃላም ግኑኝነቱን ለማደስ ያልፈነቀለው ድንጋይም ኣልነበረም፤ ጳጳሱንና ቄሱን መስቀል ኣስይዞ፣ የነርወይ ቤተክርስትያናትን ተማልዶ፣ ጋዜጠኞችን በመረብ ድልድይ ላይ እጅ አጨባብጦ ወደ ነበርንበት ሊመልሰንና ክህደቱን በጥሞና ሊያያዘው ነበር። እዚህ ከታሪክ መማር ያለብን ነገር የትግራይ መሬት ዘሎ ወይም ሕዝብዋን ወደ ኃላ ትቶ ከኤርትራ ጋር እርቀሰላም ይፈጠራል ማለት ከንቱ ኣስተሳሰብ መሆኑ ነው። ፕሮፌሰር ዳንኤል ግንኙነቱን ከናፈቁና በኣስቸኳይ ከፈለጉ ደግሞ ከኤርትራ ትውልድ የተውጣጣው የመለስ መንግሥት ጋር ግንባር መፍጠር ይችላሉ፤ መለስም የሳቸውን ድጋፍ እንደሚሻ እርግጠኛ ነኝ።

> ሠ- "በከፈቱት ጦርነት ምክንያት 100000 የሚሆን ድሃ ገበሬ እና ወዛደር በከንቱ ደሙን አፈሰሰ። በዚህም ጦርነት በኢትዮጵያ በኩል በኣብዛኛው ያለቁት አማራዎች፣ ኦሮሞዎችና አፋሮች ነበሩ።" ይላሉ ፕሮፌሰር እንግዴህ።

"ድሃ ገበሬና ወዛደር" ሲሉ እንግዴህ በኢትዮጵያ በኩል የሞተው ያን ያህል ነው ማለት ነው። እንዲህ የመሰለ ልቃሚ ኣሃዝ ተጠቅመው እኛን ሊያስረዱ መሞከራቸው ኣሳፋሪ ነው። የሚያሳፍረው ነገር ያን ያክል ብዛት ያለው ሞተ የሚባለው ኣሃዝ ማውራቱ እሳቸው የመጀመርያው ባይሆኑም የሞተው ሁሉ በጅምላ ኢትዮጵያዊ እንደሆነ በግድየለሽነት እንደ እውነት መቀበላቸው ብቻ ሳይሆን ኣብዛኛው የሞተውም ከሌላ ብሄረሰብ እንደሆነና ትግሬው እቤቱ ደጃፍ ቁጭ ብሎ ይመለከት እንደነበር ኣድርገው ማቅረባቸው ነው። በኤርትራ በኩል የሞተውስ ያውቁታል? እንደ እኔ ከሆነ በኢትዮጵያና ኤርትራ የተካሄደው ጦርነት የብሄረሰቦች የተናጠል ጦርነት ኣለመኖሩን ታሪኩ እንደ ኣዲስ መመርመር ይኖርባቸዋል እላለሁ።

መለስ ዜናዊ በዚህ ወር መጀመርያ ለኣስመሪኖ ድረገፅ ባለቤት በኣዲስ ኣበባ ቤተ መንግሥት ጋብዞ በሰጠው ቃለ መጠይቅ ላይ ከጦርነቱ ዋዜማ ኢትዮጵያ የነበራት ወታደር ተበታትኖ 50 ሺህ ብቻ እንደ ነበር ኣምኖኣል። ኤርትራ ብያንስ 150 ሺህ እንደነበራትም ይገልፃል። ለወረራ በከባድ ዝግጅት እንደ ነበረችም ሁላችን እናውቀዋለን። እሱ እንዳመነበትም በኤርትራ ድንበር ወታደር የሚባልም ነገር ኣልነበረም። ከኣንድ ዓመት በላይ በፈጀ የኢትዮጵያ መከላከያ ሓይልን የማደራጀት ጊዜ ሲሞትና ሲሰዋ የነበረ የትግራይ ምሊሻና ህበረተሰብ በጠቅላላ ነው። ሌላው የትግራይ ወጣት ባለበት ሁሉ እየተፈተሸ ተለቅሞ ወደ ጦር ሜዳ ተወስዶ ብዙ ሂወቱን ሰውቶኣል። ቁስለኛ ከጋለ ጦርነት መሃል ሲያወጣና ምግብ ለሠራዊቱ ሲያቀብል ወዶም ተገዶም ኣለ ምንም መከላከያ ሃገራዊ ሃላፊነቱ ሲፈፅም የተሰዋ

ሰላማዊና የኣካባቢው ነዋሪ ዜጋ ብዙ ነው። በተረፈ ስለ ሞተው ብሄረሰብ ብዛት የትኛው እንደሆነ የመለያየቱ ርካሽ ፖለቲካ ግን ለዳንኤል ክንዴ እተወዋለሁ።

ረ- “ታላቋ ትግራይ ዓረና (ጀግናዋ) ትግራይ” ሲሉ የታላቅዋ ትግራይ ልዩ ቀመርም ፈጥረዋል። የኢትዮጵያን መነጣጠል ያሳሰባቸው የዓረና መሪዎችና ኣባላት ድርጅታቸው የሰየሙት ይህን የሚያመለክት ሲሆን (ሉዓላዊነት)፣ ካንኤል ክንዴ ማሳመን እንደሚሞክሩት፣ ዓረና ከታላቅዋ ትግራይ ጋር ምንም ግኑኝነት የለውም።

በመጀመርያ፣ እንዲሁ በግብተኝነት ከመናገር ይልቅ ‘ዓረና’ ምን ማለት እንደሆነ ኣንዲት ቃል ጠይቀው መረዳት በቻሉ ነበር፤ እንኳንስ ትግርኛ የኣገራቸው ቋንቋ የባዕድ እንግሊዘኛም ተምረዋልና። ‘ዓረና’ ማለት ጀግና ማለት ኣይደለም፤ “ምዕራይ” ማለት ፈር መያዝ፣ ወደ ኣንድ መሥመር መግጠም፣ መተባበር ማለት ነው። የዓረና ትግራይ ድርጅት ኣሰያየም የመለስ ዜናዊ ስርዓት በጎጥ የከፋፈለውን የትግራይ ህብረተሰብ የማዋሃድ ቀና ዓላማ ያለው ይመስለኛል። ሆን ብለው ይሁን ወይም ባለማወቅ የሚፈጥሩት ትርጉም ግን የተወራውን በቁሙ ለሚደግም የኣከራሪው ማህበረሰብ የብሄረሰብ ጥላቻ ቋንቋን ሊያዳብር ይችል ይሆናል።

እዚህ ላይ ይህን ግኑኝነት በመፍጠር መላውን የትግራይ ሕዝብ እንደጠላት የማስቀመጥ ስልት በመዘርጋት ላይ እንዳሉ እናያለን። ዓረና ትግራይን የሚደግፍ ሁሉ ደግሞ (ግማሽ የትግራይ ሕዝብም ቢሆን) ትግራይን ሊገነጥል ነው እያሉ በጠላትነት በመፈረጅ ተከታዮቻቸውን ማስተማር ጀምረዋል።

በተለይ ስለ እየታነፁ ነው የሚሉዋቸው “የታላቋ ሪፓብሊክ ትግራይ” ዝግጅት ቅናት ይሁን ቅዠት ሊገባኝ ኣይችልም። በትግራይ የተደረገ ልዩ ነገር በሌሎች ያልተደረገ የሚያንገፈግፋቸው ኣዲስ ነገር ምንድነው? ትግራይ ባትገነጠል ዩኒቨርሲቲ ኣያስፈልጋትም ማለት ነው? ሑመራ ኣይሮፕላን ማረፍያ መሥራት “ከሪፓብሊክ ትግራይ” ጋር ምን ኣገናኘው? ሑመራ ለሰሊጥ የውጭ ሽያጭ ካልሆነ በስተቀር ከሌሎቹ ከተሞች እንኳን ኣትወዳደርም።

ወደ ገዳርፍ የሚሰራው መንገድስ ዳንኤል ክንዴ ዓሰብ ዓሰብ አትበሉ የሚሉን ውጭ የሚላከው የእርሻ ሰሊጥ የመሰለ ውጤት በየት ሊላክ ነው? እንግዲህ የመለስ ዜናዊ መንግስት በባህር በር እጦት ምክንያት በብዙ ውጥረት ላይ ስላለ በከንያም፣ ጂቡቲም፣ ሱዳንም፣ በየቦታው መንገዶች ሲቦጫጭር እንመለከታለን። የሚሉት የገዳርፉ መንገድ ደግሞ ከጎንደር ጋርም ይገናኛል።

እንደ ፕሮፌሰሩ የፖለቲካ ፍልስፍና ከሆነ ትግራይ ለማደግ መገነጠል ይኖርባታል ማለት ነው። እንጂ ከኢትዮጵያ ጋር እያለች እድገት ኣይፈቀድላትም። ወይስ ለትግራይ ብቻ የተደነገገ ካለፉት ሥርዓቶች የተወረሰ የመሓል ኣገር ኣስቀያሚ ፖለቲካ ማብቃት የለበትም ነው የሚሉት? በመስፍናዊ ስርዓት የቅናት፣ የክፋት፣ ተንኮልና፣ ቅጥፈት ስነልቦና ባለንበት መዋዕልም በህብረተሰቡ በተለይ በሙሁሩ ክፍል ያንሰራራ በመሆኑ ይህ ኣይነት የብሄረሰብ ጥላቻ ለፈፋ ግንቦት 7 በዋናነት ተያይዞታል። ግንቦት 7 በቁጥር 63 ሓምሌ 30 ላይ ባወጣው ፅሁፉ መሠረት ወያኔ በዘረኛ ኣድላዊነቱ ለትግራይ (ወታደር ሳይሆን) ምልሻ በየወሩ 500 ብር ከ1991

እስከ 1993 ይከፍል እንደነበር ያመለክታል። በጦርነቱ የተካፈሉ የቅርብ ዘመዶች ባይኖሩኝ ወይም ይኸን የፈጠራ ወሬ ከሩቅ የምቀበል ሰው ብሆን ኖሮ ለማመን ችግር ባልነበረብኝ። ፅሁፉ ከዛ ይቀጥልና በኤርትራው ጦርነት ምክንያት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወታደር በትግራይ ስለሰፈረ ህብረተሰቡ በዳቦ ሽያጭ ምን ያህል እየተጠቀመ እንዳለ በቀን የ800 ሺህ ዳቦ ፍጆታ ስሌት የኢኮኖሚ ትንታኔ ያቀርባል። እንዲህ ያለ አስገራሚ ትንታኔ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ካልሆነ በስተቀር በሌላ ዓለም ታይቶም አይታወቅ! እንግዲህ የወታደር ዳቦ ቀለብ ሽያጭ ጥቅም ለተቀረው ህብረተሰብ እንዲዳረስ ግንቦት 7 የሻዕቢያ ጦር አዲስ አበባ እንዲገባ እንዴት ሳይጋብዝ ቀረ? የፕሮፓጋንዳ ፅሁፉ በትግራይ ሕብረተሰብ ላይ ያነጣጠር የተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ የመለስ ዜናዊ ስርዓትን ሳይሆን በትግራይ ላይ በጠላትነት እንዲነሳሳ የሚቀሰቅስ ነው። የዚህ ድርጅት ዓላማና የሚከተለው አቅጣጫ በኢትዮጵያ ላይ ምን አይነት ውድቀት እየተበተበ መሆኑ ለመገንዘብ በድረገጹ ስለ አገሪቱ የሚቆረቆር ሁሉ እንድያነበው አስፈላጊ ነው እላለሁ። ለተቀረው የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ የሚያስተላልፉት መልእክት ዓላማው ለስልጣን ይሁን ለሌላ በትግራይ ወገኑ ላይ የጥላቻ መርዝ በመንዛት የብሄረሰብን ግጭት የሚቀሰቅስ ነው። እንደ እኔ ከሆነ፣ ስልጣን ለመያዝ የሚንደረደሩ በግንቦት 7 ያሉ ሰዎች ከተሳካላቸው ኢትዮጵያ ህልውናዋን ከፍተኛ ስጋት ላይ የሚጥሉ ገና የኃላ ችግሮች ናቸው።

ከዚሁ አኳያ የፕሮፌሰር ዳንኤል ትግራይን የመገንጠል ሂደት የትግራይ ህዝብ ወይም እንደ ዓረና የመሰሉ ድርጅቶችን ከመለስ መንግሥት (ሆን ብለው ይመስላል) ለይተው አያስቀምጡም። እዚህ መገንዘብ ያለብን ጉዳይ ግን ለመገንጠል እየተዘጋጀ ያሉት መለስና ተባባሪዎቹ ከሆኑ ካለ ከፋፋይ የብሄረሰብ ፖለቲካ የሚያራምዱና የሚያስገነጥሉ አክራሪ ሓይሎች አስተባባሪነት የሚሳካ አይደለም። ይህን አይነት ፖለቲካ የሚያራምዱ ግለሰቦች ደግሞ መረዳት ያለባቸው ኢትጵያዊነት አስተሳሰቡ ጭምር እንጂ ስለተወለዱበት ብቻ ለኢትዮጵያዊነት በቂ አለመሆኑ ነው።

እዚህ ላይ ዳንኤል ክንዴ ይህን ሁሉ ስለ ትግራይ ወይም "ወያኔ" ሲያትቱ ሊደብቁት ያልቻሉት የወሰዱት ፀረ-ትግራይ አቋም በመግብያቸው ላይ አስቀምጠውታል፤ ይኸውም፣ "**እነዚህ አመታት ራስን በጥሞና የመፈተሻና የመመርመሪያ፣ እንዲሁም ጠላትና ወዳጅን የማወቂያ ዓመታት ሆነው መቆጠር ይኖርባቸዋል።**" ኤርትራ ከተገነጠለች ወዲህ ማለታቸው ነው እንግዲህ፤ ትግራይን ከኤርትራ በማብጠርጠር ለይተው የግኑኝነቱን አመሠራረት መጣል የፈለጉት። ይህ ማለት ጠላቱ ትግራይ እንጂ ኤርትራ አይደለም ነው በሳቸው አሰተሳሰብ። ስለ ትግራይ በኤርትራ ፈደረሽን ውይይት መሓል ያለ አግባብ በማስገባት ሰዉን ሲነዘንዙ "የቆጡን አወርዳለሁ ብላ የብብትዋን ጣለች" የተባለች ሴትዮ አይነት ሆነው እናገኛቸዋለን። ትግራይን ከያዘችው ስፍራ በማሽቀንጠር ኤርትራን ወደ መአዱ መጋበዝ ብልህ አካሄድ ወይም ኢትዮጵያዊነት አይደለም።

እንግዲህ ኢትዮጵያን ከዳርዳርዋ እየሸራረፉ የብሄረሰብ የሽኩቻ ፖለቲካ በማእከላዊነት የሚያራምዱ ትግራይን ዒላማ የሚያደርጉና ኤርትራን በስትራተጅያዊ ወዳጅነት የሚፈርጁ ሓይሎች በአገር ውስጥና ውጭ አንድ ግንባር

በመፍጠር ሂደት ላይ እንዳሉ እናያለን። የዚሁ እንቅስቃሴ ዋና የጠላት ረድፈኞች የሆኑት ከላይ እንዳመለከትኩት ያለውን መንግሥት ተቃዋሚ ነን የሚሉ ከሻዕቢያ ጉያ ስር ተሸጉጠው በባርነት የሚኖሩ ድርጅቶች ናቸው። እንዳየነው የትግራይንና ኤርትራን ዒላማ ያደረገ ይህ ዓይነት ፖለቲካ እውቅና ወይም ነፍስ የሚዘሩለት ምሁራን በይፋ እየተቀላቀሉት እናያለን። እነዚህ ሰዎች በብሄረሰብ ጥላቻና ፖለቲካ በመታወራቸው ብዙውን ጊዜ ትምህርት ከእውቀትና እውነት ጋር ሆድና ጀርባ ሆኖባቸዋል። በተለይም ኣርበኝነት ለነሱ ባእድ ነገር ስለ ሆነ ወዳጅ ከወገን መለየት ኣይችሉም።

ለዚሁ እንቅስቃሴ እውጭ ኣገር የገቢ ምንጮቻቸው የሆኑ ብዙ ኣክራሪ ወይም የዋህ ኢትዮጵያውያንም የመለስ ዜናዊን መንግሥት ለመጣል ይህን የኤርትራ ዝምድናን ኣስፈላጊነት ማራመድ ይሞክራሉ። በተለይ ግንቦት 7 ወደዚሁ ኣፍራሽ የብሄረሰብ ፖለቲካ ከተቀላቀለ ወይም ዓላማውን ካሳወቀ ወዲህ ከውጭ የሚያገኘው የኢትዮጵያውያን ድጋፍ ከኣንድነት ፓርቲ መነጠሉና ለሰላማዊው እንቅስቃሴ የመዳከም ምክንያት መሆኑ የሚካድ ኣይመስለኝም። የውጪ የኢትዮጵያውያን የዲሞክራስያዊ እንቅስቃሴ ትግልም ኣቅጣጫውን ስቶ በብሄረሰብ ከፋፋይ ፖለቲካና ትጥቅ ትግል መሃከል ውዥንብር ውስጥ ገብቶ በተስፋ ቆራጥነት ሲዋልል ይገኛል።

ክፍል ሁለት በኢትዮጵያና ኤርትራ ግኑኝነት ላይ በመጪው ይቀጥላል

መልእክት ወደ ፀሃፊው በዚህ መጠቀም ይቻላል- lgebre@live.ca